# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 186 ህዳር 28 2004 ገጽ 1

በአኬልዳምኛ "ሽብርተኛ" ማለት አገር ወዳድ፤ ነፃነት ወዳድ፤ ፍትህ ወዳድ ማለት ነው። በአኬልዳምኛ ሽብርተኛ መሆን ክብር ነው።

ግንቦት 7 ፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በመለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ "ሽብርተኛ" መባል የሕዝባዊነትና የአርበርኝነት ኒሻን እንደሆነ ተረድተን ትግላችንን በበለጠ ጥንካሬና ቁርጠኝነት እንድናፋፍም ጥሪ ያደርጋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በዘረፋ ከአገር የሚያሸሸው ገንዘብ መጠን 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር መድረሱ ተጋለጠ

በዘረኛው መለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ገዢ ጉጇሌ ቁንጮዎች እንደ አውሮጵያዊያኑ ዘመን አቆጣጠር ከ2000 እስከ 2009 ባለው የ9 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ብቻ ከ 11 ቢሊዮን 700 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ በህገወጥ መንገድ ከአገር በማሸሽ በውጪ አገር ባንኮች በግል ሂሳባቸው እንዳከማቹ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት መርሀግብር ሥር ጥናት ያካሄደው "ግሎባል ፋይናንሻል ኢንተግሪቲ" የተባለው አለማቀፍ ተቋም ባወጣው የቅድመ ዳሰሳ ሪፖርት አጋለጠ።

ጥናቱን ባካሄደው ተቋም መረጃ መሠረት:- በስርቆት፣ በሙስናና በተለያዩ ህገወጥ መንገዶች የተገኘ ነው የተባለው ይህ ትልቅ መጠን ያለው ገንዘብ፤ መለስ ዜናዊ እራሱ በተገኘበት አለም አቀፍ መድረክ ከዛሬ 6 ወር በፊት ይፋ ከሆነው 8 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ጋር ሲነፃፀር በ3 ነጥብ 26 ቢሊዮን ብልጫ ያለው መሆኑም በጥናቱ ተገልጧል። ይህ 3ቢሊዮን 260 ሚሊዮን ዶላር በአንድ አመት ጊዜ ማለትም የቀድሞው ሪፖርት ባልሸፈነው የ2009 ዓም ብቻ የተዘረፈ መሆኑ ጥናት አድራጊውን ተቋም ሳይቀር አስደንግጦአል።

በአለም በድህነት ከመጨረሻዎቹ አገሮች ተርታ ከሆነቺው አገራችን ተሰርቆ በውጪ አገር ባንኮች የተደበቀው ይህ ገንዘብ ምንጩ፤ ለልማት፤ ለድህነት ቅነሳና ለሰብአዊ እርዳታ ከምዕራባዊያን አገሮች የተገኘ እንደሆነ ሲታወቅ ባለሥልጣናቱ በጫረታ፤ በሙስናና በዘረፋ ገንዘቡን አጭበርብረው በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ሥም ከባህር ማዶ በከፈቱት ባንኮች ያሸሹት እንደሆነም ተገልጾአል።

አሥራ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ማለት በአገራችን ገንዘብ ሲመነዘር ከ187 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሆነ ሲታወቅ፤ ይህ ደግሞ በምድር ላይ ሊሠራ ወደሚችለው ልማት ቢተረጎም መለስ ዜናዊ ሥልጣን ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ ባለፉት 20 አመታት 80 ቢሊዮን ብር በማውጣት 27 ሺ ኪሎሜትር መንገድ ሰርቻለሁ በማለት የሚነዛውን ጉራ ከእጥፍ በላይ በማሳደግ፤ መላውን የአገሪቱን ገጠሮች በአቅራቢያቸው ካለው ትላልቅ ከተሞች ጋር ማገናኘት የሚችል 60 ሺ ኪሎሜትር ርዝመት ያላቸው መንገዶችን መገንባት የሚችል ነበር።(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በበረከት ስሞኦን ቁጥጥር ሥር ያለው ብአዴን በግምገማ እየተተራመሰ ነው። ለአገዛዙ ያልተመቹ ሁሉ በግንቦት 7 አባልነት እየተፈረጁ መሆኑ ተዘገበ

ዘረኛው መለስ ዜናዊ በበላይነት በሚመራው ህወሃት ሥር ተቀጥያ በመሆን ላላፉት 20 አመታት የህወሃትን ጸረ አማራ ፖሊሲ ሲያስተገብሩና ሲያስፈጽሙ የኖሩ በዚህም የተነሳ የገዛ ወገኖቻቸውን ህዝብ መከራና ሲቃይ ዕድሜ ሲያራዝሙ የቆዩ የብሄረ አማራ ድርጅት የክልልና የዞን አመራርና አባላት በሌላ ዙር ግምገማ እየተተራመሱ መሆኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከባህር ዳር ባስተላለፈው ዜና ገለጸ።

በአማራ ክልል ያሉትን አባላት በግምገማ የማተራመሱ ሥራ የተጀመረው ፤ በክልሉ ያሉ ወጣቶች ቁጥሩ እየጨመረ በመጣው የሥራ አጥነትና የኑሮ ውድነት እጅግ እየተማረሩ በአገዛዙ ላይ የሚያሰሙት ግልጽ ተቃውሞ በአደባባይ ላይ መሰማት በመጀመሩ፤ በክልሉ ታምቆ ከኖረው ጸረ ወያኔ ስሜት ጋር ተዳምሮ ባልተጠበቀ ሰዓት ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቅስ ይችላል ተብሎ ስለተሰጋ፤ ነባር የብአዴን አባላትን በሙስናና በዲስፒሊን ሰበብ ከሥራ አሰናብቶ ወጣቶችን ሥራ ለማስያዝ እንቅስቃሴ በመጀመሩ ነው ተብሎአል።

ከበረከት ስሞኦንና ከአዲሱ ለገሰ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው አንዳንድ የክልሉና የዞኑ ብአዴን አመራር አባላት በሙስና የተዘፈቁ መሆናቸው እየታወቀ ለበርካታ አመታት ዝም ሲባሉ እነደነበረ የዘገበው ዘጋቢያችን፤ በሙስና የአስተዳደር በደል ውስጥ እጃቸው ያልገባው በርካታ አባላቱ እንደማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል በኑሮ ውድነቱ እየተሰቃዩ በመሆናቸዉ በአገዛዙ ላይ የምር ተቃውሞ እያሰሙ መምጣታቸው አገዛዙ ያልጠበቀው ሌላ እራስ ምታት እንደቀሰቀሰበት ገልጾአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የሽብረተኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የስልክ ና የኢሜል መልእክቶችን ለመጥለፍ እንዲሁም ዬሳተላይት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ለማፈን የሚጠቅመውን ቴክኖሎጂ ከህንድና ከቻይና ኩባንያዎች መግዛቱን ዊኪሊክስ አጋለጠ

ዊኪሊክስ በዋጣው አዲስ መረጃ በአለም ላይ ለዚሁ ተግባር የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚሸጡ የ150 ኩብንያዎችን ስም ይፋ አድርጓል።

የዊኪሊክሱ መስራች ባለቤት የሆነው ዊሊያም አሳንጂ ለ ዘ ታይምስ ኦፍ ኢንዲያ እንደተናገረው፤ አንድ የህንድ ኩባንያ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የስለላና የማፈኛ መሳሪያዎችን ለኢትዮጵያ መንግስት መሸጡን ከኩባንያው ፋይል አንብቤአለሁ" በማለት አጋልጠዋል።

ሀይማካል ፕራዴሽ የተባለው የህንድ ኩባንያ የሳተላይት መስመሮችን፣ ከኢንል ሳት፣ ኢዩቴል ሳት፣ አረብ ሳት፣ ቱርክሳት የሚተላለፉ የሲና የኬዩ የቴሌቬዥንና የራዲዮ የሳተላይት ስርጭቶችን እንደሚያፍን ዘ ሂንዱ የተባለው የህንድ ጋዜጣ ዘግቧል። በዊኪሊክስ መረጃ መሰረት የማፈኛና የስለላ ቴክኖሎጂዎችን ለአምባገነን መንግስትታ ከሚሸጡት የህንድ ኩባንያዎች መካከል ሾጊ ኮሚኒኬሽን፣ ክሊር ትሬል፣ ሺልድ ሴኩሪቲ የሚገኙበት ሲሆን፣ የቻይናዎቹ ዜድ ቲኢ፣ ሀዋይ ቴክኖሎጂና ቪክስቴልም ተጠቅሰዋል።

13 ሚሊዮን ዜጎቿ ከአለም አቀፉ ህብረተሰብ በሚለገሰው የእርዳታ እህል ህይወቱን የሚገፋባት አገር ኢትዮጵያ ን እየገዛ ያለው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በብዙ ሚሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ በማፍሰስ የህዝብን ስልክና የኢንተርኔት አገልግሎቶችን ለመጥለፍ እንዲሁም ሰተላይት ሬዲዮኖችንና ቴሌቪዥንኖችን ለማፈን ሙከራ እንደሚያደርግ በተደጋጋሚ ተዘግቧል።

ዊሊያም አሳንጂ አምባገነን መንግስታት ስልጣናቸውን ለማቆዬት ሲሉ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በማፍሰስ እነዚህን የረቀቁ ቴክኖሎጂዎች እንደሚገዙ በድረገጹ ላይ አስፍሯል።

## በጸረ ኢትዮጵያ አቋሙ በህዝብ ዘንድ የተጠላው ህወሀት፤ የድርጅቱን ታሪክ በአዲስ መልክ ለማፃፍ 43 ሚሊዮን ብር መመደቡ ተጠቆመ

የ"ከአገር በስተጀርባ" መጽሐፍ ደራሲን በመጥቀስ ፍኖተ-ነፃነት እንዳስነበበው፤ የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆነው ሰሎሞን ዕንቋይን "ጠልመት" እና የሀይላይ ሀድጉ ሥራ የሆነውን "ንንዓት" የተባሉትን መጽሀፍት መሰረት በማድረግ፤ የህወሀትን ታሪክ በአዲስ መልክ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ለማፃፍ 43 ሚሊዮን ብር ተመድቧል።

"የሀብት ብዛትና ስልጣን እውነተኛውን ታሪክ ሊቀይሩት አይችሉም" ያሉት የመጽሐፉ ደራሲ፤ "43 ሚሊዮን ብር ቀርቶ 43 ቢሊዮን ብር ቢመደብ፤ የህወሀት ሀጢአት ከቶ ሊሸፈን አይችልም"ብለዋል።

በተለየ መልኩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህወሀቶች መረጃና ምንጭ የማይገኝላቸውን አዳዲስ የፈጠራ ታሪኮችን በብዛት በመጻፍና በመጽሀፍ መልክ በማሳተም ወደ ገበያ ማስገባት መጀመራቸው ይታወቃል።

ሰዎችም ሆነ ድርጅቶች አቅምና ጥንካሬ እያጡ ሲመጡና በራስ መተማመናቸው ሲጠፋ በታሪክ ውስጥ ወደመሸሸግ እንደሚያዘነብሉ አያሌ ጥናቶች ያመለክታሉ።

ህወሐት የአማራውን የባህል ተጽኖ መከላከልና ለረጅም ጊዜ በስልጣን ላይ መቆዬት የሚቻለው፣ የድርጀቱን ታሪክ እና የክልሉን ባህል በማስፋፋት ነው የሚል ፖሊሲ ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ይታወቃል።

ህወሀቶች በቅርቡ የአጼ ሚኒሊክን ዝና ዝቅ የሚያደርግ ታሪክ ጽፈው አቅርበዋል። እነ ስብሀት ነጋ የሚመሩት አዲስ ታሪክ የመፍጠር እንቅስቃሴ በህዝቡ ውስጥ ቅሬታ እየፈጠረ መምጣቱም ይታወቃል።

ጋዜጠኛ ፋሲል ሞገስ በአውራምባ ታይምስ ላይ ወጣቱ አሥር አይነት የኢትዮጵያን ታሪክ እየተማረ መሆኑን እና ታሪኩም እርስ በርሱ እየተጋጨበት መምጣቱን ገልጾ መጻፉ ይታወሳል።

## “ሽብርተኛ”፤ “በአኬልዳምኛ” - ለእኩልነት የሚታገል አርበኛ!

*በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልችልም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልችልም!!! እኔ ለእናንተ አርዓያ ለመሆን እሞታለሁ!!! እናንተ ታግላችሁ ነፃ ውጡ!!!*

እነዚህ ነበሩ በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ተማሮ በራሱ ላይ እሳት የለኮሰው የመምህር የኔሰው ገብሬ የመጨረሻ ቃላት። እነዚህ ቃላት በአዕምሮዎቻችን ውስጥ እየጮሁ እረፍት ነስተውናል። እውነትም ግፍና መከራን እየተቀበሉና እያዩ እንዴት መኖር ይቻላል?

የእርምጃው ግዝፈትና የመልዕክቱ ክብደት ነው የየኔሰውን ዜና እረፍት በመላው ኢትዮጵያና ከኢትዮጵያም ውጭ ከመቅጽበት እንዲሠራጭ ያደረገው። መምህር የኔሰው ገብሬ ራሱን በእሳት ማቃጠሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ የደረሰበት የምሬት ደረጃ ገላጭ ነው። የመለስ ዜናዊ አሽከሮች መምህሩን የአዕምሮ ሕመምተኛ ለማስመሰል መሞከራቸው ዜናውን አባባሰው፤ የመለስ ዜናዊን አረመኔነት አጎላው።

ከመምህር የኔሰው በኋላም እዚያው ዳውሮ ዞን ተርጫ ከተማ ውስጥ አንድ ሌላ እጩ መምህር በደረሰበት የአስተዳደር በደል ተማርሮ በትምህርት ቢሮ ግቢ ውስጥ በሚገኝ ዛፍ ላይ ራሱን ሰቅሎ ለመግደል ሞክሮ የነበረ መሆኑ ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ደወል ነበር።

መምህር የኔሰው ገብሬ ወደ ሁላችንም አዕምሮ የላከውን ይህንን ጠንካራ መልዕክት ለማደብዘዝ ሲሉ ነው የመለስ ዜናዊ ተላላኪዎች “አኬልዳማ” የተሰኘውን ውስጠ-ባዶ ጯሂ ፊልም ያቀነባበሩልን።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለመለስ ዜናዊ ጆሮ ጠቢዎች የማይመች መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ለዚህ ፊልም ምላሽ መስጠት አስፈላጊ አይደለም። መለስ ዜናዊ ንቀት በወጠረው ቁጥር ለሚያሰማቸው የውሸታሙ እረኛ “ቀበሮ መጣብኝ!!!” ጩኸቶች የኢትዮጵያ ህዝብ ጆሮ መስጠት ካቆመ ውሎ አድሯል።

ያም ሆኖ ግን “የአኬልማ” አዘጋጆች ባልጠበቋቸው ምክንያቶች የፊልሙ መታየት ጠቀሜታ ያለው ሆኖ ተገኝቷል። እስቲ ከቻሉ ፊልሙን ደግመው በጥሞና ይመልከቱና ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይስጡ።

- ሽብርተኛ ማነው?
- ሽብርተኛ እንዴት ያለ ሰው ነው?

በፊልሙ “ሽብርተኛ” ተብለው የሚጠሩ ሰዎች የታወቁና የተከበሩ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። እነዚህ ዜጎች የሚታወቁት ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለዲሞክራሲ በመቆማቸው ነው። እነዚህ ሰዎች ፍቅርን እንጂ ጥላቻን ሲሰብኩ አልተሰሙም።

ስለዚህም “አኬልዳማ”

*“ሽብርተኛ” ማለት የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አገዛዝ በመቃወም ለሕዝቦች ነፃነትና እኩልነት የሚታገል ኢትዮጵያዊ ማለት ነው።*

የሚል ትርጉም ይሰጣችኋል።

“ሽብርተኛ እንዴት ያለ ሰው ነው?” ለሚለው ጥያቄም የፊልሙ ምላሽ

*“ሽብርተኛ” ቅን፣ ትሁትና ህሊናው የሚገዛው ሰው ነው።*

የሚል ምላሽ ታገኛላችሁ።

ታድያ “በአኬልዳማ” ትርጉም መሠረት ሽብርተኛ መሆን የማይፈልግ ማነው? በአኬልዳማ ትርጓሜ መሠረት ሽብርተኛ መሆን የማይፈልግ ዘረኛ፣ ሆድ-አደር፣ አድርባይ፣ ብልጣ ብልጥ እና ፈሪ ነው።

የኢትዮጵያ ወጣቶች እና አዛውንቶች፤ ወንዶችና ሴቶች በዘረኞች፣ በሆድ-አደሮች፣ በአድርባዮችና ፣ በብልጣ ብልጦች እና ፈሪዎች የሚደርስባቸውን ወከባ ተቋቁመው በአኬልዳምኛ ሽብርተኛ ሆነው ራሳቸውንና አገራቸውን ነፃ ማውጣታቸው አይቀሬ ነው።

በአኬልዳምኛ “ሽብርተኛ” ማለት አገር ወዳድ፤ ነፃነት ወዳድ፤ ፍትህ ወዳድ ማለት ነው። በአኬልዳምኛ ሽብርተኛ መሆን ክብር ነው።

ግንቦት 7 : የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በመለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ “ሽብርተኛ” መባል የሕዝባዊነትና የአርበርኝነት ኒሻን እንደሆነ ተረድተን ትግላችንን በበለጠ ጥንካሬና ቁርጠኝነት እንድናፋፍም ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

.....................................................................................................

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በዘረፋ ከአገር የሚያሸሸው ገንዘብ መጠን 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከዚህም በተጨማሪ የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ያስችል ይሆናል በሚል ስሌት ያለምንም ጥናትና ዕቅድ በህዝብ ላይ የተጫነውን የአባይ ግድብ መዋጮ 54 ቢሊዮን ብር በቀላሉ በመሸፈን በተቀረው 133 ቢሊዮን ብር ፤ ከ4 ሚሊዮን በላይ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚፈልጉትን ወገኖች፤ በአሁኑ ጊዜ በምግብ ለስራ ፕሮግራም የታቀፉትን ከ7 ሚሊዮን በላይ ዜጎች፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በሌሎች ከተሞች ጎዳናዎች ላይ ወድቀው በቆሻሻ ገንዳዎች ላይ ምግብ እየለቀሙ የሚኖሩትን ዜጎች ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማቋቋም እንደሚያስችል መረጃዎች ያመለክታሉ።

ህብረሰተቡን እያስመረረ ያለው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዬው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረትም እንዲሁ በከፍተኛ ደረጃ ይቀንስ እንደነበር ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ይህንን ጥናት ያካሄደው የተባበሩት መንግሥታት የልማት ተራዲኦ አካል የሆነው ተቋም "የኢትዮጵያ ህዝብ በዝርፊያ የተነሳ ደሙ ሁሉ ተመጥቶ አልቋል፣ ከማለት አልፎ ፣ "ኢትዮጵያዊያኖች ከድህነት ለመውጣት የቱንም ያክል ቢፍጨረጨሩ፣ አሁን በሚታዬው ዝርፊያ ወደ ታች የሚፈስን ወንዝ፣ ወደ ላይ በመዋኘት ለመጨረስ ሙከራ እንደማድረግ ይቆጠራል።" ሲል የመለስ አገዛዝ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ አሰልፋታለሁ እያለ በየጊዜው የሚያውራውን ወሬ ተረት ተረት አድርጎታል።

በሙስና ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተዘፍቀው ገንዘባቸውን በውጭ አገር ባንኮች በማስቀመጥ ላይ የሚገኙት በአብዛኛው እራሱ መለስ ዜናዊና ባለቤቱ አዜብ መስፍንን ጨምሮ ከፍተኛ ስልጣን የተቆናጠጡ ጥቂት የህወሀት ጄኔራሎችና ባለስልጣናት ናቸው።

አቶ ኤፍሬም ማዴቦ በቅርቡ ባወጡት ጥናታዊ ጽሁፍ አሁን ይፋ የሆነው ተጨማሪ 3 ነጥብ 26 ቢሊዮን ዶላር ሳይካተት ባለፈው የተባበሩት መንግሥታት ሪፖርት ይፋ የሆነው ከኢትዮጵያ የተዘረፈውን 8 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ወደ አገር ቤት ቢመለስ ለአባይ ግድብ ማሰሪያ የሚዋጣውን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሸፍኖ፣ 90 የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ 18 ዩኒቨርሲቲዎች፣ 27 ኮሌጆች፤ 36 ዘመናዊ ሆስፒታሎች፤ 180 ጤና ጣቢያዎች፤ 6 የዘይት ፋብሪካዎች፤ 4 የስሚንቶ ፋብሪካዎች እንዲሁም አራት እጅግ ከፍተኛ የሚባሉ አግሮ ኢንደስትሪዎችን ለማቋቋም ያስችላል።

በትራንስፎርሜሽን እና እድገት ስም የመለስ አገዛዝ ባለፉት 10 አመታት ብቻ ከቻይናና ከህንድ መንግስታት ከ 25 ቢሊዮን ዶላር በላይ መበደሩን ቀደም ተብሎ መዘገቡ ይታወሳል። የመለስ ባለስልጣናት ለሚያካሂዱት ዘረፋ ፣ መጪው ትውልድ ከፍሎ የማይጨርሰው እዳ ውስጥ እየገባ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት 10 ዓመታት በሙስና ወደ ውጭ ባንኮች የፈሰሰውን ገንዘብ ለመቆጣጠር ተችሎ ቢሆን ኖሮ ፣ የኢትዮጵያ የዚህ አመት በጀት 300 ቢሊዮን ብር ይደርስ እንደነበር ኢሳት ከባለሙያዎች ያገኘውን ሙያዊ ትንበያ አስደግፎ ዘግቦአል።

እንደኢሳት ዘገባ በከፍተኛ ደረጃ ዝርፊያ ከሚካሄድባቸውና የኦዲት መስሪያቤቶችን የምርመራ ውጤት ለመቀበል ፈቃደኛ ከማይሆኑት መስሪያ ቤቶች መካከል ደግሞ መከላከያ ሚኒስቴር አንዱ ነው።

በሳሞራ የኑስ የሚመራው መከላከያ ሚኒስቴር፣ ለጦር ጀኔራሎችና ለህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት እቃዎችን ያለቀረጥ እንዲያስገቡ በማድረግ፣ ከፍተኛ ዝርፊያ እንደሚያካሂድ ኢሳት በቅርቡ በሰራው የዶኩመንታሪ ፊልም ማጋለጡ ይታወሳል።

በሌላ በኩል ጉምሩክ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ መብራት ሀይል እና ዋና ዋና የገንዘብ ምንጭ የሆኑ ተቋማትን የተቆጣጠሩት፣ የህወሀት ባለስልጣናት፣ ከመስሪያ ቤቶች ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እየዘረፉ ነው እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። የወያኔ ባለሥልጣናት የለየለት ዘረፋ ላይ የተሰማሩት ከምርጫ 97 ወዲህ ሲሆን፣ አሁንም ድረስ ተጡዋጡፎ መካሄዱን የፋይናንሻል ኢንተግሪቲ ዘገባ ያመልክታል።

የአለም መንግስታት በአለም እጅግ ደሀ ከሆነችው እና በምጽዋት ከሚያኖሩዋት ኢትዮጵያ፣ ይህን ያክል ገንዘብ መዘረፉን ከሰሙ በሁዋላ የሚያወጡት መግለጫ በጉጉት እየተጠበቀ ነው ተብሎአል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ቱርክ ላይ ዘረኛው መለስ ዜናዊ በተገኘበት ታላቅ አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ ያጋለጠው 8 ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ዘረፋን አስመልክቶ ወያኔ ሹሞች እስከዛሬ ቃል እልተነፈሱም።

ሰሞኑን ይፋ የተደረገው ሪፖርት አዘጋጆች " ኢትዮጵያውያን እዬደሙ ነው በማለት" የዝሪፊያውን አስከፊነት በሪፖርታቸው ላይ አስፍረዋል።

## ኃጥዓን በሠለጠኑ ግዜ ህዝብ ያልቀሳል!!!

በአገራችን ውስጥ ህዝብ ማልቀሱን አላቆመም። መለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛና ነውረኛ ቡድን በስልጣን ላይ ከተቆናጠጠ ወዲህ ደግሞ ሮሮው በጥልቀት ልቅሶው በስፋት ቀጥሏል። በኢትዮጵያችን ውስጥ ህዝብ ያዘነበትና የተከፋበት ዘመን እንዲህ እንደ መለስ ዜናዊ ዘመን ያለ አልታየም።የሮሮው ጥልቀት የኤሰው ገበሬን የመሰለ ዜጋ በራሱ ላይ ላምባ አርከፍክፎ እንዲቃጠል አድርጎታል። ይሄ ብዙ ዜጎችን አሳዝኗል።አስለቅሷል።

አዎን በአገራችን ላይ እግዜርን የማያውቁ ክፉ ኃጥዓን ቡድኖች ተነስተል። የእነዚህ ቡድኖች ድርጊትም ህዝብን ከዳር እስከዳር እያስለቀሰ ነው። ክፉ ድርጊታቸውም ድንበር ተሻግሮ የሩቅ ሰዎችን ጭምር እያሳዘነ ነው።

የአንድ አገር ህዝቦች ባንድነት እንዳይቆሙ ተፋቅረውና ተሳስበው እንዳይኖሩ ሆን ብሎ የሚለያዩበትን መንገድ መፍጠር ኃጢዓት ነው። ወንድምን በሃሰት አስመስክሮ በሃሰት አስፈርዶ ስቃያቸውን ማብዛት ኃጢዓት ነው። በኃይማኖት ድርጅቶች መካከል ጠብና ክርክር ተፈጥሮ ደም እንዲፈስ ማድረግ ኃጢዓት ነው። ይህን የመሰሉ ኃጢአቶች በህወት ሲፈጸሙ ከርመዋል። አሁንም እየተፈጸሙ ነው።መለስና ይህ ክፉ ዘረኛ ቡድኑ ስልጣን ላይ እስካሉ ድረስ እንዲህ ያሉ ኃጢአቶች በአገራችን ላይ ሲፈጸሙ ይኖራሉ።

በዓለማችን ላይ ህዝብ የህዝብ ጠላት የሆነበት ግዜ ታይቶ አይታወቅም። መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ግን አማራ የትግራይ ህዝብ ዋነኛ ጠላት ነው ብለው ጽፈው ለትውልዱ አስቀምጠውለታል። ይህንንም እንዲመስክርላቸው ሃውልት አስቀርጸው አቁመዋል። ኦሮሞ አማራን ሊበቀል የተዘጋጀ እንደሆነ አድርገው ሲሰብኩ ሁለት አስርተ ዓመታትን አስቆጥረዋል። ይህም እውነት እንደሆነ ለማስመለስ በክፉም በደጉም አብረው በኖሩ አማሮችና ኦሮሞዎች መካከል ብጥብጥ ፈጥረው የብዙ ንጹሃን ደም እንዲፈስ አድርገዋል። እንዲህ በየቦታው አብሮ በኖረ ህዝብ መካከል ጥላቻን እየሰበኩ የዜጎች ደም በከንቱ እንዲፈስ ማድረግ ኃጢዓት ነው።መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ግብራቸው ኃጢዓት ሁኖ አብሮአቸው የከረመ ስለሆነ ክፉ ምግባራቸውን እንደ ጽድቅ እየቆጠሩት በደስታ ሰክረው ይኖራሉ። አገሪቷ እንዲህ ባሉ ቡድኖች በተያዘች ወቅት በእነመለስ ዜናዊ መንገድ አለመሄድ ብጹእነት ነው።

ሌላው ህዝብን የሚያቀያይሙበትና ደም የሚያፋስሱበት መንገድ ኃይማኖት ነው።ሙስሊምና ክርስትያን አብሮ ተፋቅሮና ተከባብሮ የሚኖርባት ጥሩ አገር ኢትዮጵያ ነበረች። መለስና ዘረኛ ቡድኑ ስልጣነ መንበሩን ከተቆናጠጡ በኋላ በሁለቱ ታላላቅ ኃይማኖቶች መካከል ጠብ ተፈጥሮ ብዙ ደም ፈሷል። ህወሃት በፈጠረው መሰሪ ተንኮል ምክንያት በሃይማኖት ምክንያት ግጭት ተፈጥሮ በጎንደር፤ በወሎ፤ በአዲስ አበባ፤ በጂማና በመሳሰሉት ቦታዎች የብዙ ንጹሃን ደም ፈሷል። መለስ ዜናዊ ግን ራሱ በፈጠረው ግጭት የሚገለውን ገድሎ የሚያስረውን አስሮ ዜጎችን አስለቅሶ ወንበሩን እንደያዘ ቀጥሏል። እንዲህ በወንድማማቾች መካከል ጠብንና ክርክርን መዝራት ክፉ ኃጢዓት ነው። እግዚአብሄር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች አሉ ሰባተኛውን ግን ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች። እርሷም በወንድማማች መካከል ጠብን የሚዘራውን ነው።ምሳሌ 6 ቁጥር 19.

በገዛ አገራችን ውስጥ ወንድም ወንድሙን በሃሰት እንዲከስ፤ አንዱ በአንዱ ላይ በሃሰት እንዲመሰክር ሲደረግ የአንድ ትውልድ ዘመን ተቆጠረ።" ነገራችሁ እውነት ከሆነ እውነት ሃሰት ከሆነ ደግሞ ሃሰት ይሁን" የተባለው የታላቁ መጽሃፍ ቃል ክብር እንዳይኖረው ሁኗል። ፍትህን እንዲያስጠብቁ የተሾሙ አቃቤ ህግያን ሆን ብለው ዜጎችን በሃሰት ከሰው በሃሰት አስመስክረው የሞት ፍርድ ሲያስፈርዱ የፍትሁን ሥርዓት በኩኔኔ እየተኩት መሆኑን እንዳይገነዘቡ እዝነ ልቦናቸው በዘረኝነትና በሴሰኝነት በሽታ ደንዝዟል። እንዲህ የፍትሁን ሥርዓት ማዋረድ ለአገራችንም ለትውልዱም አይበጅም ያሉ እውነተኞችና በጽድቅ እንቁም ያሉ የሚዋረዱበት ሃሰተኞችና በክፉ ሥራዎቻቸው የበረቱ የሚሾሙባት የሰው ዘር ምድረ በዳ እንድትሆን እየተደረገች ነው።

መለስና ግብረ አበሮቹ አገራችንን አዋርዶ፤ ድንበሯን አፍርሶ፤ ምድሪቱንም ሸንሽኖ ለባእዳን አሳልፎ ሰጥቶ፤ ፍቅራችንንም አጥፍቶ ዘመኑን ሁሉ ለመኖር ምኞት አለው። እንዲህ ያልተመኘ ክፉ አምባገነን የለም።ጋዳፊ እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ለመረዳት አእምሮው ደንዝዞ ነበር። ሆሲኒ ሙባረክም እንዲሁ ብዙ ዘመን አእምሮው ማስተዋል ተስኖት ነበር።መለስ ዜናዊ ከእነዚህ አምባገነኖች ለመማር እምቢ ብሎ የንጹሃንን ደም እንዲሁ በከንቱ እያፈሰሰና ክፉ ሃሳብን እያፈለቀ አገራችንን ልንወጣ ወደምንቸገርበት አዘቅት ውስጥ እየነዳት ነው።

ማንም ኩነኔን የሚጸየፍና ጽድቅን የሚፈልግ መለስ ዜናዊንና ግበረ አበሮቹን በሚችለው ሁሉ መዋጋት አለበት። ግንቦት ሰባትም አገራችን የእውነትና የጽድቅ አውድማ እንድትሆን መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ለፍርድ እስከሚቀርቡ ድረስ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። እነዚህ ኃጥአኖችንም ለመገለበጥ ቆርጦ እየሰራ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## መቀመጫውን ካሊፎርኒያ ያደረገው የኦክላንድ ኢንስቲቲዩት በአሁኑ ወቅት የወያኔ አገዛዝ እየፈፀመ ያለውን ህብረተሰቡን የማፈናቀልና መሬቱን በርካሽ የመቸብቸቡን ድርጊት ኮነነ

## 75 በመቶ የመሬት ኢነቨስትመንት ዘርፉም በትግራይ ተወላጆች መያዙን ይፋ አደረገ

የኦክላንድ ኢንስቲትዩት ዳይሬክር አኑራዳ ሚታል፣ ከኢሳት ጋር ባደረጉት ልዩ የቃለመጠይቅ ቆይታ ድረጊቱ ህገወጥና በአፋጣኝ መቆም የሚኖርበት ነው ሲሉ አሳስበዋል።

ይህ የመሬት ችርቻራ ለምግብ ፍጆታ የሚውል እህልን ለማምረት በሚል ሰበብ ለውጭ ኢንቨስተሮች ሲሰጥ በኖረበት መሬቱ ላይ ሀሳብ እነዲሰጥ እነኳን ያልተጠየቀው ህብረተሰብ፣በህይወቱ ላይ ትልቅ ቀውስ እነደተፈጠረበት ነው የተናገሩት። «የውሀ አቅርቦትን አካቶ እየተሸጠ ያለውን የለም መሬት ዋጋ ብናይ የአካባቢውንና የማህበረሰቡን ሁኔታ በፍፁም ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፣ ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ መንግስት አቅም የለሹ ተፈናቃይ ህብረተሰብ ላይ እየተከሰተ ያለውን ችግር ከቁብም አልቆጠረውም » ብለዋል።

በኢትዮጵያ መሬት በመንግስት ቁጥጥር ስር ስለሚገኝ ከህብረተሰቡ ጋር የመደራደርያ መነሻ መብት እንኳን አለመኖሩን አውስተዋል። በዚህ አመት አክላሀማ ዩንቨርስቲ በአለማችን እየተካሄደ ባለው መሬት ችርቻራ ሰበብ ችግር ላይ ስለወደቁት ሀገራት ባወጡት ልዩ ሪፖርት፣ ኢትዮጵያን በተመለከተ፣ የመሬት ሊዝ ይዞታ በሀገሪትዋ ያለውን የምግብ እጥረት ያባብሰዋል፣ በስነምእዳር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል፣ ሀገሬው ህብረተሰብንም ዘሩ እነዲጠፋ የሚያደርግ ነው ብሎለታል።

ምንም እንክዋን መለስ ዜናዊ በሚሊዮን የሚቆጠር ሄክታር መሬት በሊዝ የማደሉ ሂደት በምግብ እራሳችንን ለማስቻል ይረዳናል እያለ የሚከራከር ቢሆንም አክላማ ግን በተቃራኒው ረሀብና ድርቅን የሚያባብስ ነው ሲል በጥናቱ ለማሳየት ሞክሯል።

ከዚህ አልፎ ይህ ድርጊት የህዝቡን መሰራታዊና ሰብአዊ መብት የጣሰ መሆኑንም አሳይቷል።

ይህንን የተቃወሙ የህብረተሰቡ ክፍሎቸም እንደእንስሳ እየታደኑ የድብደባና የአስገድዶ መድፈር አሰቃቂ አደጋ እየደረሰባቸው ይገኛል፣ በተደጋጋሚ የመሬት ሊዝ ሰለባ የሆነው በጋምቤላ ክልል የሚገኘው የጋምቤላ ብሄራዊ ፓርክም ባሁኑ ወቅት ካርቱሪና ሳውዲ ስታር በተባሉ በሼክ መሀመድ አላሙዲን ባለቤትነት በሚታወቁ ካምፓኒዎች ደኑ ተጨፍጭፎ፣ ወድሞ በቁጥጥራቸው ስር መዋሉ ታውቋል።

ሌላው በግርምት የሚያስደምመው ጉዳይ ደግሞ በጋምቤላ ከተያዘው ሰፊ መሬት ውስጥ 75 በመቶ የሚሆነው ከህወሃት ጋር ቁርኝት ባላቸው የትግራይ ተወላጆች መሆኑ ነው። እንደ አክላማ ኢንስቲቲዩት ጥናት በጋምቤላ አገሬውን አፈናቅለው መሬት የተቸራቸው የትግራይ ተወላጆች ፤ ወለድ የማይከፈልበት የብድር አገልግሎት ከመንግሥት ባንኮች እየተመቻቸላቸውና የያዙትን ቦታ ያለምንም ክፍያ እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን በአካባቢው ያሉትን ኢንቨስተሮች ተዘዋውሮ ያነጋገሩት የኦክላንድ ኢንስቲቲዩት ዳይሬክር አኑራዳ ሚታል አረጋግጠዋል።

የዳይሬክተሯን የአኑራዳ ሚታልን ምስክርነት የሰሙ ኢትዮጵያዊያን ባረጉት ግምገማ፤ የሥር ዓቱ ደጋፊ የሆኑ የትግራይ ተወላጆች በተለያዩ ክልሎች በመሄድ መሬት እንዲይዙና ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚበረታቱበት ዋናው ምክንያት በእጃቸው የገባውን የፖለቲካ ስልጣን መከታ በማድረግ ኢኮኖሚውን በመቆጣጠር ስልጣናቸውን እስከወዲያኛው እናዘልቃልን በሚል ስሌት ነው ብለዋል።

### በበረከት ስሞኦን ቁጥጥር ሥር ያለው ብአዴን በግምገማ እየተተራመሰ ነው። ለአገዛዙ ያልተመቹ ሁሉ በግንቦት 7 አባልነት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የበርካታ አባላቶቹ ልብ መክዳት ያሳሰበው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት እምነት ሊጣልባቸው የማይችሉቱ ተባረው በምትካቸው ትምህርታቸውን ከከፍተኛ ትምህረት ተቋማት ጭምር አጠናቀው ለአመታት ሥራ አጥ ሆነው የተቀመጡት እየተመለመሉ እንዲገቡና የመንግሥት ሥራ እንዲሰጣቸው እንቅስቃሴ በመጀመሩ፤ የእርምጃው ሰለባ በሆኑት ነባር አባላትና ውሳኔውን በሚያስፈጽሙ አመራሮች መካከል ከፍተኛ የሆነ ግጭት ተፈጥሮአል።

በምስራቅ ጎጃም የምርጫ 97 ውጤት ተጭበርብሮአል ተብሎ እንዲጣራ በተወሰነበት ወቅት የዳኝነት ሥልጣኑን በመጠቀም ፍርድቤት የሰጠውን ውሳኔ ገልብጦ ለወያኔ ታማኝነቱን ያስመሰከረውና ለበረከት ስሞኦን ቀረቤታ እንዳለው የሚነገርለት የሺጥላ እምሩ የተባለ፤ በአሁኑ ሰዓት የምስራቅ ጎጃምና የአዛ ዞን የጸረ ሙሲና ኮሚሽን ሃላፊ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኘው የብአዴን አባል ሰሞኑን በግምገማ ስም ከሃላፊነቱ ተወግዶ በቁም እስር ላይ እንደሚገኝ ዘጋቢያችን አረጋግጦአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ወያኔ ህዝብን ለማስፈራራት ሲል በ3 ተከታታይ የቴለቪዥን ዝግጅት ያሰራጨውን የፈጠራ ድራማ በጽኑ የሚኮንን መግለጫ አወጣ

አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ህዳር 20 ቀን 2004 ዓም በ "አኬልዳማ " ድራማ የህዝብን የዲሞክራሲና የለውጥ ጥያቄ ማዳፈን አይቻልም" በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ፤ "ደርግን የተካው ኢህአዴግ ትምህርት ወስዶ የተሻለ ስርዓት ይገነባል ተብሎ ቢጠበቅም፣ እሱም በተራው የለየለት አምባገነንና አፋኝ ስርዓት ለመሆን ብቅቶአል። በዚህም ምክንያት ጭቆና እንዲወገድ፣ እኩልነት እንዲረጋገጥና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲመሠረት በሚድረግ ጥረት ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች ለሀገራቸው ልማትና ብልፅግና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ከመስራት ይልቅ ጥላቻና አምባገነንነት የአገዛዙ የአመራር ዘይቤ ሆኖአል" ብሎአል።

ደርግ ህወሓትን “ወንበዴ”፣ “ፀረ-ሰላም” እና “አስገንጣይ” የሚል ስም ሰጥቶት እንደነበር ይታወቃል" ያለው የአንድነት መግለጫ፤ ህወሓት/ኢህአዴግም በተራው ተቀናቃኞቹን “ፀረ-ሰላም”፣ “ፀረ-ልማት” እና “አሸባሪ” ለማለት ወግ ደርሶታል ካለ ቦኋላ "አገዛዙ ትላንት ካሳለፈው የትግል ልምድ ሊማር ያለመቻሉን በግልፅ እንረዳለን፤ የሕዝብን ጥያቄ በሰላይ ጋጋታና በወታደር ብዛት ማዘግየት እንጂ መጨፍለቅ እንደማይቻል ከኢህአዴግ በላይ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ድርጅት ሊኖር ባልቻለ ነበር ሲል የመለስ ዜናዊ በጠመንጃ ጋጋታ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም መዳከር ከንቱ እንደሆነ አስገንዝቦአል።

ወያኔ በዜጎች ላይ እየወሰደ ባለው አፈናና በህጋዊነት ተመዝግበው በመንቀሳቀስ ላይ ባሉት የፓርቲው አመራርና ተራ አባላት ላይ እየተፈጸመ ያለው ጥቃት ያስቆጣው የአንድነት ፓርቲ ፤ "አገዛዙ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተቃዋሚ አባለትና ጋዜጠኞች ላይ ሰፊ የእስርና የአፈና እርምጃ አጧጥፎ ቀጥሎበታል ፤ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትንና የነፃው ሚድያ አባላትን ወደ እስር ቤት መወርወርና ማዋከብ የአገዛዙ የቀን ተቀን ስራ ሆኖአል በማለት ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ ብዛት ያላቸው ጋዜጠኞች ለእስርና ለስደት እንደተዳረጉ ፤ በዚህም የተነሳ በቅርቡ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ማኔጅግ ኤዲተር ዳዊት ከበደ ከሀገር ለመሰደድ እንደቻለ ገልጾአል፡፡

በጸረ ሽብርተኛ ህግ ተብዬው አዋጅ ህዝብን የፍርሃት ድባብ ውስጥ ለመክተት መለስ ዜናዊ፤ በረከት ስምዖንና ሽመልስ ከማል እየሰሩት ያለው ድራማ ከንቱነትን አስመልክቶ፤ "አገዛዙ በአሸባሪነት ስም እየወሰደ ያለው ቅጥ ያጣና ነውረኛ ርምጃ በዜጎች ዓይን ተቀባይና አሳማኝ ሊሆን እንዳልቻለ ተረድቷል ያለው የአንድነት መግለጫ፤ "አገዛዙ ከህዝብ ያጣውን ተቃባይነትና አመኔታ ያገኘ መስሎት ርካሽ የሆነ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ሕዝብን ለማሳመን አቅዶ ተነስቷል ብሎአል።

"የሕዝብን ጥያቄ በሰላይ ጋጋታና በወታደር ብዛት ማዘግየት እንጂ መጨፍለቅ እንደማይቻል ከኢህአዴግ በላይ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ድርጅት ሊኖር አይችልም፡" የሚለው አንድነት፣ በቅርቡ “አኬልዳማ” በሚል ርዕስ የቀረበው በጥላቻና በሸብር የተሞላ መርዘኛ የሆነ ፕሮፓጋንዳ በአንድ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ ተገኝቶ በቂ ማሰረጃ ይዘን ነው ያሰርነው ላላውና ይህንንም ተከትሎ በተለያየ ሁኔታ ለሚደርሰው ነቀፌታና ተፅዕኖ ድጋፍ ለመስጠት፤ በሌላ መልኩ ደግሞ በኑሮ ውድነትና በመልካም አስተዳደር ዕጦት የተማረረ ህዝብ በሰሜን አፈሪካና በመካከለኛው ምስራቅ ያለውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ፈለግ ይከተላል በሚል ፍርሃት ቀድሞ ለማስፈራራትና ወዮልህ ለማለት፤አልሞ የተነሣ ነው፡ "ሲል ገልጣል።

አንድነት አያይዞም የኢ.ቲ.ቪ. የሶስት ቀናት ፕሮፓጋንዳ እርስ በርስ የሚቃረን፣ በጥላቻ የታጨቀና ግልፅ የስም ማጥፋት ወንጀል የተፈፀመበት፣ የአንድነት ፓርቲ አባላት ያልሆኑ ግለሰቦች እንደ ፓርቲው አባላት አድርጎ ያቀረበ ነው ሲል ኮንኖታል።

በመቀጠልም "ከዚህ ቀደም ብዛት ያላቸው የኢህአዴግ አባላትና አመራሮች ወደ ኦነግ ከመግባታቸው በተጨማሪ የደንህነትና የመከላከያ አባለት የነበሩ ዜጎች በገፍ ወደ ኦነግና ግንቦት 7 የገቡበት ሁኔታ እንዳለ የአደባባይ ምስጥር ነው ያለው የአንድነት መግለጫ በኢ.ቲ.ቪ. እይታና አመክንዮ ከተሄደ ኢህአዴግም ሆነ መከላከያ ሰራዊቱ አሸባሪዎች ናቸው ማለት ነው" በማለት የአንድነት ፓርቲ አባላት በሚተዳደሩበት ግልፅ ህገ-ደንብ መሠረት አንድ የአንድነት ፓርቲ አባል የሆነ ሰው የሌላ ፓርቲ አባል መሆን እንደማይችል አስታውቆአል፡፡

ወያኔ በአንድነት ፓርቲ ላይ እያካሄደ ያለው የሥም ማጥፋት ዘመቻ ያንገሸገሸው አንድነት፤ "ፓርቲያችንን በአሸባሪነት ስም ጥላሸት እየቀቡ ከሕዝብ ለመነጠል የሚደረግ እኩይ ተግባር ሊቆም ይገባል " በማለት ያስጠነቅቅና፤ አገዛዙ በእንዲህ ዓይነቱ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ከሕዝብ የማገኘው ጥቅም አለ ብሎ ካሰበ ተሳስቷል፤ የኢ.ቲ.ቪ. እንዲህ ዓይነት በጥላቻ የታጨቀ አሰነዋሪና የወረደ ዘገባ ማስተላለፉም ከፍተኛ የሆነ የዕውቀት፣ የስነ ምግባርና የሞራል ውድቀት ላይ እንደሚገኝ ማሳያ ነው "ብሎአል።

አያይዞም ህወሓት በረሃ በነበረበት ዘመን ባንክ ይዘርፍ እንደነበር በየአደባባዩ በኩራት እንደሚናገር እየታወቀ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሌሎችን በዚህ መክሰሱ ጉዳዩን አስቂኝ አድርጎታል ብሎአል።

“አኬልዳማ” የተባለው የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ በፍርድ ቤት የተያዘን ጉዳይ በቴሌቭዥን ፍርድ የተሰጠበት ተግባር መሆኑን የሚያስታውሰው አንድነት ፣ አገዛዙ በህግ ሳይሆን በራሱ ሚዛን አሻባሪ ብሎ ዜጎችን የሚፈርጅ ከሆነ፣ የፍርድ ቤት አስፈላጊነት ምኑ ላይ ነው? የፍርድ ቤት ነፃነትስ ከየት ይመጣል? ሲል ይጠይቃል።

የኢህአዴግ አሰኳል የሆነው ህወሓት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በኤርትራ ጉዳይ ላይ እያራመደው ያለው አቋም ሀገራችንን ትልቅ ዋጋ ማስከፈሉን፣ ሀገራችንን ወደብ አልባ እንድትሆን ያደረገው፣ ስልጣንን እንጂ የሀገርን ጥቅም ማዕከል አድርጎ ያለመሄድ በሽታ መሆኑን ያወሳው ፓርቲው፣ ኢህአዴግ ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት በቁርጠኝነት የሚታገለውን አንድነት ፓርቲን ከሻቢያና ከሽብርተኝነት ጋራ ለማገናኘት መሞከር ታላቅ ስህተት ከመሆንም አልፎ ይህን ክስ ለመሰንዘር የሞራል ብቃት የለውም፡፡ ሲል አጣጥሎታል።

አገዛዙ የሕዝብን የለውጥ ፍላጎት በስለላና በጦር ኃይል እጨፈልቃለሁ የሚል አምባገነናዊ አካሄድ የቁልቁል ጉዞ እንደሚወስደው የሚጠቅሰው አንድነት ፓርቲ ፣ የኢህአዴግ አባላትም አመራሩ እየተንደረደረ እየሄደበት ካለው የመቀመቅ ጉዞ፣ ሀገርንም ፓርቲውንም አይጠቅምምና ተመለስ ሊሉት ይገባል ሲል ምክሩን ለግሷል።

በመጨረሻም ፓርቲው "የአገዛዙ ሟርተኛ ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን የሚያሸብርና ወደ ደም መቃባት የሚወሰድ የእልህ ጉዞ መሆኑን ጠቅሶ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገራችን ካለችበት የፖለቲካ አዙሪት አንድትወጣ ከፍርሃት ራሳችንን አውጥተን እጅ ለእጅ ተያይዘን ለዴሞክራሲና ለህግ የበላይነት የሚደረገውን ትግል እናግዝ ሲል ጥሪ አቅርቦአል።

### በበረከት ስሞኦን ቁጥጥር ሥር ያለው ብአዴን . . . (ከገፅ 3 የዞረ)

ይህ በዚህ እንዳለ ወያኔ አገር አቀፉን የመምህራን ማህበር አፍርሶ በምትኩ ታማኝ አባላቶቹ የሚመሩት ማህበር በክልል ደረጃ ካዋቀርበት ጊዜ ጀምሮ በአማራ ክልል መምህራን ማህበር ውስጥ በመንቀሳቀስ የክልሉ መምህራን ማህበር ፕሬዝዳንት ለመሆን የበቃውን መምህር መንግስቱ አህመዴን፣ ከስልጣን ለማስወገድ ወያኔ ዘመቻ መጀመሩን ለማወቅ ተችሎአል።

እንደምንጮቻችን መረጃ ወያኔ መምህሩን ከስልጣኑ ለማስነሳት የፈለገው ናዝሬት ተካሂዶ በነበረው አለማቀፍ የመምህራን ጉባኤ ላይ "የመምህራንን የደሞዝ ጭማሪ፣ የደረጃ እድገትንና የማስተማርና ሀሳብን የመግለጽ መብቶች ፣ ከሁሉም በላይ መምህራን ከፖለቲካ ተጽእኖ ነጻ እንዲሆኑ፣ በሰለማዊ ሰልፍ ሳይቀር መብታቸውን እንዲጠይቁ ሊፈቀድላቸው ይገባል" የሚሉ ሀሳቦችን በመሰንዘሩ እንደሆነና እርሱ ያቀረበው ሃሳብ ለውይይት አለመቅረቡ አበሳጭቶት ስብሰባውን ረግጦ በመውጣቱ ነው።

መምህር መንግስቱ አህመዴ የኢህአደግ አባል እንደሆነ ሲታወቅ የመምህራንን መብት መከበርንና የመማር ማስተማር ነጻነትን አስመልክቶ ከአለቆቹ ጋር እየተጋጨ በመምጣቱ በበርካታ መምህራን ዘንድ አድናቆትና ፍቅር ለማተረፍ የበቃ እንደሆነ ይነገርለታል።

በአማራ ክልል የመምህራን ፕሬዝዳንት አቋም ያልተደሰቱ የወያኔ ባለስልጣናት በተለያዩ የወረዳ ትምህርት ቤቶች ተገኝተው "የማህበሩ ሊቀመንበር የግንቦት7 አባል ነው፤ መምህራን የተቃውሞ ሰልፍ እንዲያደርጉ እና ከመንግስት ጋር እንዲጋጩ እየቀሰቀሰ ነው" በማለት ግለሰቡን ለማጥቃት ቅስቀሳ እንደጀመሩበት ተያይዞ የደረሰን ዜና አረጋግጦአል።

ሆኖም የክልሉ መምህራን ከሊቀመንበራቸው ጎን በመቆም "የማህበሩ ሊቀመንበር ከስልጣን የሚወገድ ከሆነ፣ መምህራን የራሳቸውን እርምጃ ይወስዳሉ" በማለት በማስጠንቀቃቸው ና በአቋማቸውም በመጽናታቸው አገዛዙ ያሰበውን እርማጃ ለመውሰድ እንደተደናገጠና፣ ነገር ግን ከአገር አቀፉ መምህራን ማህበርም ሆነ ከሌሎች ንኡስ ማህበራት ጋር እንዳይገናኝ እንዳደረገው ታውቆአል።

በአማራ ክልል የብአዴን አባላት መካከል በተነሳው ክፍፍል በቅርቡ መሳሪያ በመማዘዝ እስከመጋደል የደረሱ እንደነበሩና በጎንደር ከ180 በላይ አባላት በፈቃዳቸው ከአባልነት መሰናበታቸውና አብዛኛዎቹ ለድርጅቱ የነበራቸውን ታማኝነትና ታዛዝነት ትተው አገዛዙን በማማረር እንደተጠመዱ መዘገባችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org